# የናዛሪን ቤተ ክርስቲያን የውስጥ መተዳደሪያ ደንብ

## የናዛሪን ቤተ ክርስቲያን ማዕከላዊ እሴቶች

ናዛሪን ቤተ ክርስቲያን ዋና ዋና የሚባሉ የእምነት አንቀጾችና ማዕከላዊ እሴቶች እንደሚከተሉት ናቸው።

<u>እኛ ክርስቲያኖች ነን</u> - የኢየሱስን ጌትነት ከሚመሰክሩ እውነተኛ አማኞች ጋር አንድ ነን። እግዚአብሔር እኛን በጣም ከመውደዱ የተነሳ አንድያ ልጁን ኢየሱስ አዳኛችን እንዲሆን እንደሰጠን እናምናለን። በኢየሱስም የመስዋዕትነት ሞት የተነሳ ሁሉም ሰው የሀጢያት ይቅርታን እንዳገኘና ከእግዚአብሔር ጋር ከታረቅን በኋላ በመካከላችንም እርቅ እንደሆነ እናምናለን። ከእግዚአብሔር ጋር ከታረቅን በኋላ በመካከላችንም እርቅ እንደሆነ እናምናለን። እግዚአብሔር እኛን በወደደን መጠን እርስ በእርሳችን ልንዋደድ ይገባል። እንዲሁም እግዚአብሔር ይቅር ባለን ልክ እኛም ሰዎችን ይቅር ልንል ይገባል። መጽሐፍ ቅዱስ የእውነት ሁሉ ምንጭ እንደሆነ እናምናለን። በዌልዝልያን የቅድስና ትውፊት ውስጥ የምንገኝ ሲሆን የክርስትና እምነት ታሪካዊ የእምነት መግለጫዎችን እንቀበላለን።
<u>እኛ የቅድስና ህዝቦች ነን</u> - እግዚአብሔርን ለማምለክ እና እግዚአብሔርን በሙሉ ልባችን ፣ነፍሳችን፣አእምሮአችን እና ሀይላችን ለመውደድ እንዲሁም ባልንጀራችንን እንደራሳችን ለመውደድ በመጽሐፍ ቅዱስ እና በእርሱ ጸጋ የተጠራን ሰዎች ነን። በምንሰጠው ከእምነት የሆነ የአገልግሎታችን ምላሽ የተነሳ መንፈስ ቅዱስ ቀን በቀን የፍቅር እና መንፈሳዊ ባህርይ ያለን፣ ስነ ምግባራዊ የሆንን እና ተግባራዊ ቅድስናችንን የጠበቅን፣ርሁሩሆች እና ፍትህን የምንሻ ዓይነት ሰው እንድንሆን ይለውጠናል። በውስጣችን የእግዚአብሔር መልክ የሚያሳየው እና በውስጣችን የክርስቶስን ባህርይ የሚፈጥረው መንፈስ ቅዱስን ነው። በአማኞች ውስጥ የሚታየው ቅድስና በግልጽ ክርስቶስን መምሰልን ነው።
<u>እኛ ተልዕኮ ያለን ህዝቦች ነን</u> - ተልዕኮአችንም ወደ አለም ሁሉ በመሄድ ክርስቶስን የሚመስሉ ደቀ መዛሙርትን ማፍራት ነው። ተልዕኮአችን የምንጀምረው ለአምልኮ በአንድ ላይ ስንሰባሰብ እና ወደ አለም ሁሉ ስንሄድ ነው። ተልዕኮአችን አዳዲስ አማኞችን ወደ ህብረታችን መቀበልና አዳዲስ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናትን መጀመር ነው። ተልዕኮአችን የእግዚአብሔር ፍቅር ጌታን ለማያውቁ ሰዎች ማካፈል እና ለድሆች የእርሱን ርኅራሄ ማሳየት እና ለተጎዱ ሰዎች የሚያስፈልጋቸውን ነገር በማድረግ እግዚአብሔርን ርኅራሄ ማሳየት ነው። ሰዎችን ወደ ጌታ ለማምጣት ፍላጎታቸውን ለማሟላት እንዲሁም የጌታን ስም የሚጠሩ ሰዎችን ሁሉ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለማካተት የተሰጠን ነው። እግዚአብሔር እንድንሰራው የሰጠንን ተልዕኮ መወጣት እንድንችል መሪዎችን ለማፍራት ለማሰልጠንና ለማስተማር የተሰጠን ነን።

<u>የናዛሬን ቤተ ክርስቲያን የአባላት መመሪያ</u>
ይህ ትንሽ ጽሁፍ የተዘጋጀው የናዛሬን ቤተ ክርስቲያን አባላት የናዛሬን ቤተ ክርስቲያን እንዴት ስራዋን እንደምታከናውን በቂ መረጃ ለመስጠት ነው። ህጋዊ (ኦፊሴላዊ) የቤተክርስቲያኗ መመሪያ የቤተክርስቲያን መመሪያ ተብሎ የሚታወቅ ነው። የቤተክርስቲያን መመሪያው በጣም ህጋዊ ስርዓቶች የበዙበትን እና በጣም ትልቅ የሆነ ነው። ብዙ ሰዎች በተለይም የእንግሊዝኛ ቋንቋ ሁለተኛ ቋንቋቸው የሆኑ ሰዎች በመመሪያው ውስጥ ያሉት ቃላት በጣም አስቸጋሪ እንደሆኑ ይናገራሉ። ይህቺ ትንሽ መጽሐፍ ግን ቀላል እንግሊዝኛን በመጠቀም ከአጥቢያ ቤተ ክርስቲያናትና ከቀጠናዎች ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ነገሮች በአንድነት አጣምራ ይዛለች። በቅንፍ ውስጥ ያለው ቁጥር የሚያመለክተው በቤተ ክርስቲያኗ መመሪያ (2009-2011) የሚገኝበት ክፍል ነው። ስለዚህም ሰዎች

አስፈላጊ ሆኖ ካገኙት ከመመሪያው ጋር ማነጻጸር ይችላሉ።

<u>ተልዕኮ(ሚሽን)</u> - የናዛሪን ቤተ ክርስቲያን ተግባር ክርስቶስ በሚሰጠው ልብ መንጻትና የሀጢያት ይቅርታ አማካኝነት የሚፈጸመውን የእግዚአብሔርን የሚለውጥ ጸጋ ለሰዎች ሁሉ ማሳወቅ ነው። ቀዳማዊ ተልዕኮአችን ሰዎችን ‹‹ክርስቶስ መሰል ደቀ መዝሙር ማድረግ›› አማኞችና በህብረትና በአባልነት (ማህበረ ምዕመናን) ማደራጀትና የእምነት ምላሽ የሚሰጡትን ሁሉ ለአገልግሎት ማስታጠቅ (ማስተማር) ነው። ‹‹የአማኞች ህብረት›› ዋነኛ አላማ በመጨረሻው ቀን ሰዎችን ሁሉ በክርስቶስ ፍጹም አድርጎ ወደሚያቀርበው ወደ ክርስቶስ ማቅረብ ነው።
ደህንነት ፣ፍጹም ማድረግ፣ማስተማርና ሚሲዮናዊ መላክ የሚካሄደው በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ነው። የክርስቶስ አካል የሆነቸው አጥቢያ ቤተክርስቲያን የእምነት ተልዕኮ መግለጫ ነች። እነዚህ አብያተክርስቲያናት በአስተዳደራዊ አሰራር ቀጠናዎችና ክልሎች ተደርገው ይዋቀራሉ።

## <u>የዕምነት አንቀጾች</u>

### I. አሀዱ-ሥሉስ አምላክ

1. ለዘላለም ህልው ሆኖ በሚኖር ፣መጨረሻ በሌለውና ሉአላዊ ፈጣሪና የአለማት ገዥ በሆነው፤እርሱ ብቻ ገዢ (ፈጣሪና አስተዳዳሪ)፣በማንነቱ ፣በባህርያቱና በዓላማው ቅዱስ፣ ቅዱስ ፍቅር እና ብርሀን የሆነ አምላክ በመሰረታዊ
ማንነቱ አሀዱ-ሥሉስ አብ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ሆኖ እንደተገለጠ እናምናለን።
(ዘፍ 1፣ዘሌ 19:2 ዘዳ 6:4-5፣ ኢሳ 5:16፣6:1-6፣ 40:18-31፣ ማቴ 3:16-17፣28:19-20፤ ዮሐ 14:6-27፤1ኛ ቆረ 8:6፤2ኛ ቆሮ 13:14፤ገላ 4:4-6፤ ኤፌ 2:13-18፤1ኛ ዮሐ 1:5፤4:8)
2

### II. ኢየሱስ ክርስቶስ

2. የአሀዱ-ስሉስ ሁለተኛ አካል የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ለዘላለም ከአብ ጋር እንደነበር፤ በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ትስብእት እንደሆነና ከድንግል ማርያም እንደተወለደ ፣ከዚህም የተነሳ ክርስቶስ የፍጹም መለኮትና የፍጹም ትስብዕት ውሁድ፣እውነተኛ አምላክና እውነተኛ ሰው፣አምላክ-ሰው እንደሆነ እናምናለን።
ኢየሱስ ክርስቶስ ለሀጢያታችን እንደሞተ፣በእውነት ከሞት ተነስቶ ስጋውን ዳግም እንደለበሰ ፣በሁለንተናው ፍጹም የሰውን ባህርይ እንደያዘ፣ ወደ ሰማይ እንዳረገና በዚያ እንደሚማልድልን እናምናለን።
(ማቴ 1:20-25፤16:15-16፤ሉቃ 1:26-35፤ዮሐ 1:1-18፤ሐዋ 2:22-36፤ሮሜ 8:3፤32-34፤ገላ 4:4-5፤ፊሊ 2:5-11፤ቆላ 1:12-22፤ 1ኛ ጢሞ 6:14-16፤ዕብ 1:1-5፤ 7:22-28፤9:24-28፤1ኛ ዮሀ 1:1-3፤ 4:2-4፤15)

### III. መንፈስ ቅዱስ

3. የአሐዱ-ሥሉስ ሶስተኛ አካል የሆነው መንፈስ ቅዱስ ሁል ጊዜም እንደሚኖርና በኢየሱስ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በትጋት እንደሚሰራ፣ ዓለምን ስለሀጢያት እንደሚወቅስ፣ ንሰሐ ገብተው ለሚያምኑት አዲስ ልደትን እንደሚሰጣቸው፣ አማኞችን እንደሚቀድስና በክርስቶስ ወዳለው እውነት እንደሚመራቸው እናምናለን።
(ዮሀ 7:39፤14:15-18፤26፤16:7-15፤ሐዋ 2:33.15:9 ሮሜ 8፤1-27፤ገላ 3:1-14፤4-6፤ኤፌ 3:14-21፤1 ተሰ 4:7-8፤ 2 ተሰ 2:13፤1 ጴጥ 1:2፤ 1ኛ ዮሀ 3:24፤4:13)

## IV. ቅዱሳት መጽሀፍት

4. ስድሳ ስድስቱ የብሉይና የአዲስ ኪዳን ቅዱሳት መጻሕፍት በመለኮታዊ እስትንፋስ-በእግዚአብሔር እንደተጻፉ ለደህንነታችን አስፈላጊ የሆነውን የእግዚአብሔርን ፍቃድ እንደሚገልጹ እናምናለን። ስለሆነም በቅዱሳት መጻህፍት ውስጥ ያልተካተተ አሳብ እንደ እምነት አንቀጽ አይወሰድም።

(ሉቃ 24፡44-47፣ዮሀ 10፡35፤ 1 ኛ ቆሮ 15፡3-4፤2 ኛ ጢሞ 3፡15-17፤1 ኛ ጴጥ 1፡10-12 2 ኛ ጴጥ 1፡20-21)(ሉቃ 24፡44-47፣ዮሀ 10፡35፤ 1 ኛ ቆሮ 15፡3-4፤2 ኛ ጢሞ 3፡15-17፤1 ኛ ጴጥ 1፡10-12 2 ኛ ጴጥ 1፡20-21)

## V. የመጀመሪያ ሐጢያትና ግለሰባዊ ሐጢያት (የውርስ ወይም የውድቅ እና የግል ወይም የድርጊት ሐጢያት)

5. የመጀመሪያዎቹ ወላጆቻችን አለመታዘዝ ኃጢአትን እንዳስከተለና ኃጢአትም ሞትን እንዳመጣ እናምናለን። ኃጢአት ሁለት መልኮች እንዳሉት እናምናለን፡የመጀመሪያው ወይም የውድቀትና tegbarawi ወይም ግለሰባዊ ኃጢያት ናቸው።

5.1. የመጀመሪያው ወይም የውድቀት ኃጢያት በአዳም ልጆች ሁሉ ላይ የደረሰ የባሕርይ መበላሸት እንደሆነ እናምናለን። ይህም ሰዎች ሁሉ ከመጀመሪያው ጽድቅ ወይም የመጀመሪያዎቹ ወላጆቻችን በተፈጠሩ ጊዜ ከያዙት ንጽህና እንዲርቁ ፣የእግዚአብሔር ጠላቶች እንዲሆኑ ፣መንፈሳዊ ህይወትን እንዲያጡ፣ ወደ ክፋት እንዲያዘነብሉና ባለማቋረጥ ይህንኑ አቅጣጫ እንዲከተሉ አድርጓቸዋል። በተጨማሪ የአማኝ ልብ በመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ሙሉ በሙሉ እስካልነጻ ድረስ የመጀመሪያው ኃጢያት አዲስ በተወለደ ክርቲያን ህይወት ውስጥ ሊኖር እንደሚችል እናምናለን።

5.2. የመጀመሪያው ወይም አዳማዊ ወይም የውርስ ኃጢያት እንደ ግል ወይም እንደ ተግባራዊ ኃጢያት ሳይሆን ለውርስ ሐጢያት መሰረት የሚጥል በመሆኑና መለኮታዊ መፍትሔው ተቀባይነት እስኪያጣ ድረስ የማንንም ተጠያቂነት የማያስከትል መሆኑን እናምናለን።

5.3. ተግባራዊ ወይም የግል ኃጢያት ስነምግባራዊ ተጠያቂነት ያላቸው ሰዎች የታወቀውን የእግዚአብሔርን ሕግ ሆን ብለው በፈቃደኝነት የሚጥሱበት እንደሆነ እናምናለን። ስለሆነም፤ የዚህ አይነቱ ሃጢያት ፈቃደኛ ሳይሆኑ በዓቅም ማነስ ምክንያት ከሚፈጸሙ ጉድለቶች፣ድክመቶች፣ስህተቶች፣ውድቀቶች ወይም ከሌሎች በውድቀት ምክንያት ከሚከሰቱ የፍጹማዊነት መመዘኛ መሰናክሎች የተለየ ነው። ይሁንና፤ እነዚህ ነገሮች ከክርስቶስ መንፈስ ጋር የሚቃረኑትንና መንፈስ ሃጢያን ተብለው ሊጠሩ የሚችሉትን አመለካከቶች ወይም ተግባራት አያጠቃልሉም። ተግባራዊ ወይም ግላዊ ኃጢያት በቀዳሚነትና በዋናነት የፍቅርን ሕግ ማፍረስ እንደሆነ እናምናለን። ከክርስቶስ ጋር በተያያዘ ኃጢያትን አለማመን ውስጥ ሊፈረጅ ይቻላል። (አዳማዊ ወይም የውርስ ወይም የመጀመሪያ ሐጢያት፤ ዘፍ 3፤ 6፡5፤ኢዮ 15፡13፤መዝ 51፡5፤ኤር 17፡9-10፤ማር 7፡21-23፤ሮሜ 1፡18-25፤5፡12-14፤7፡1-8፡9፤ 1 ኛ ቆሮ 31-4 ገላ 5፡16-25 ፤1 ኛ ዮሀ 1፡7-8)

## VI. ስርየት

ኢየሱስ ክርስቶስ በተቀበለው መከራ ባፈሰሰው ደምና በመስቀል ላይ ሞቱ አማካኝነት ለሰው ልጆች ሁሉ ሙሉ ስርየትን እንዳስገኘ፣ይህም ስርየት ብቻውን የደህንነት መሰረት ከመሆኑም በላይ ለአዳም ዘር በሙሉ እንደሚበቃ እናምናለን። ስርየቱ በእግዚአብሔር ጸጋ አማካኝነት

(በተለያየ ምክንያት ተጠያቂ ሊሆኑ ለማይችሉ) ግለሰባዊ ኃላፊነትን ለመቀበል የማይችሉትንና ንጹሀንን ልጆችን ለማዳን ሲችል ፣ከሃላፊነት ዘመን የደረሱ ንሰሐ ገብተው በማመን ይድናሉ። (ኢሳ 53:5-6፣11፤ማር 10:45፣ሉቃ 24:46-48፣ዮሀ 1:29.3:14-17፣ሐዋ 4:10-12፣ሮሜ 3:21-26፣4:17-25፣5:6-21፣1 ኛ ቆሮ 6:20 ፤2 ኛ ቆሮ 5:14-21፤ገላ 1:3-4፤ 3:13-14 ቆላ 1:19-23.1 ኛ ጢሞ 2:3-6 ፤ቲቶ 2:11-14 ፤ዕብ 2:9 ፣9:11-14፣ 13:12፣ 1 ኛ ጴጥ 1:18-21፣2:19-25 ፣1 ኛ ዮሀ 2:1-2)



## VII. ቅድመ ድነት ጸጋ ወይም ቀዳሚ ፀጋ – ነፃ ምርጫ

የሰው ልጆች በእግዚአብሔር አምሳል መፈጠራቸው ትክክለኛና ትክክል ባልሆነው ነገር መካከል ያለውን ልዩነት ተረድቶ መምረጥን እንደሚያካትት እናምናለን። ይህም የሰው ልጆች ለሚፈጽሙት ስነ ምግባራዊ ተግባር ተጠያቂዎች እንደሚሆኑ ያሳያል። በአዳም ኃጢያት ምክንያት ሰዎች ለውድቀት በመዳረጋቸው በተፈጥሯዊ ጥንካሬቸውና እምነታቸው ወደ እግዚአብሔር ሊመለሱና ራሳቸውን ሊያዘጋጁ አይችሉም። ነገር ግን የእግዚአብሔር ጸጋ በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት ለሰዎች ሁሉ በመድረስ ከኃጢያት ወደ ጽድቅ የሚመለሱ ሁሉ አምነው እንዲድኑና በእግዚአብሔር ፊት መልካምና ደስ የሚያሰኘውን ተግባር እንዲፈጽሙ ያስችላቸዋል ብለን እናምናለን።

(እግዚአብሔር መምሰልና ሥነምግባራዊ ሃላፊለት፡ ዘፍጥረት 1:26-27፣ 2:16-17፣ ዘዳግም 28:1-2፣ 30:19፣ አኢያሱ 24:15፣ መዝሙር 8:3-5፣ ኢሳ. 1:8-10፣ ኤርምያስ 31:29-30፣ ሕዝቅኤል 18:1-4፣ ሚክያስ 6:8፣ ሮሜ 1:19-20፣ 2:1-16፣ 14:7-12፣ ገላቲያ 6:7-8)

(ተፈጥሯዊ የብቃት ማነስ፡ ኢዮብ 14:4፣ 15:14፣ መዝሙር 14:1-14፣ 51:5፣ ዮሐንስ 3:6፣ ሮሜ 3:10-12፣ 5:12-14፣ 20፣ 7:14-25)

(ነጻ ምርጫን የእምለት ተግባራት፡ ሕዝቅኤል 18:25-26፣ ዮሐንስ 1:12-13፣ 3:6፣ የሐዋርያት ሥራ 5:31፣ ሮሜ 3:6-8፣ 18፣ 6:15-16፣ 23፣ 10:6-8፣ 11:22፣ 1 ኛ ቆሮንቶስ 2:9-14፣ 10:1-12፣ 2 ኛ ቆሮንቶስ 5:18-19፣ ገላትያ 5:6፣ ኤፌሶን 2:8-10፣ ፊልጵስዩስ 2:12-13፣ ቆላስይስ 1:21-23፣ 2 ኛ ጢሞቴዎድ 4:10፣ ቲቶ 2:11-14፣ ዕብራውያን 2:1-3 3:12-15፣ 6:4-6፣ 10:26-31፣ ያዕቆብ 2:10-22፣ 2 ኛ ጴጥሮስ 1:10-11፣ 2:20-22)

## VIII. ንስሐ

8. የራስን በደል ተገንዝቦ በእውነተኛ ልብ ሙሉ ለሙሉ ከሐጢአት መመለስን የሚያካትተው ንስሐ ሆን ብለውም ሆነ በድንገት በእግዚአብሔር ላይ ሐጢአት ከፈጸሙት ሰዎች ሁሉ የሚፈለግ ተግባር እንደሆነ እናምናለን። ንስሐ የሚገቡ ሰዎች ሁሉ ይቅርታ እንደተደረገላቸው አምነው ዘላለማዊ ይቀበሉ ዘንድ መንፈስ ቅዱስ የምሕረት ተስፋ ይሰጣቸዋል።

   (2 ተኛ ዜና 7:14፣ መዝሙር 32:5-6፣ 51:1-17፣ ኢሳያስ 55:6-7፣ ኤርምያስ 3:12-14፣ ሕዝቅኤል 18:30-32፣ 33:14-15፣ ሉቃስ 3:1-14፣ 13:1-5፣ 18:9-14፣ የሐዋርያት ሥራ 2:38፣ 3:19፣ :31፣ 17:30-31፣ 26:16-18፣ ሮሜ 2:4፣ 2 ተኛ ቆሮንቶስ 7:8-11፣ 1 ኛ ተሰሎን 1:9፣ ጴጥሮስ 3:9)

## IX. ጽድቅ፣ ዳግም ልደትና የልጅለት ሥልጣን

9. ጽድቅ የእግዚአብሔር የቸርነትና የዳኝነት ተግባር እንደሆነ እናምናለን። እግዚአብሔር ክርስቶስን እንደ አዳኛቸውና ጌታቸው አድርገው ላመኑት ሁሉ የሐጢአትን ይቅርታ በመስጠት እንደ ጻድቃን ይቀበላቸዋል።
10. ዳግም ወይም አዲስ ልደት እግዚአብሔር ንስሐ የሚገባውን ሐጢአተኛ የሥነምግባር ባህሪ በማንቃት ማመን፣ ማፍቀርና መታዘዝ የሚችል መንፈሳዊ ሕይወት የሚሰጥበት የቸርነት ተግባር እንደሆነ እናምናለን።
11. የጸደቀውና ዳግም የተወለደው አማኝ የእግዚአብሔርን የልጅነት ሥልጣን እንደሚያገኝ እናምናለን።
12. ጽድቅ፣ ዳግም ልደትና የልጅነት ሥልጣን እግዚአብሔርን የሚፈልግ ልብ ያላቸው ሰዎች ሁሉ በተመሳሳይ ጊዜ የሚቀበሉት ንስሐን ተከትሎ በሚመጣው እምነት አማካኝነት እንደሆነ እናምናለን። ለዚህም ሥራና የጸጋ ደረጃ መንፈስ ቅዱስ ምስክርነቱን ይሰጥል።

(ሉቃስ 18:14፣ ዮሐንስ 1:12-13፣ 3:3-8፣ 5:24፣ የሐዋርያት ሥራ 13:39፣ ሮሜ 1:17፣ 3:21-26፣ 28፣ 4:5-9፣ 17-25፣ 5:1፣ 16-19፣ 6:4፣ 7:6፣ 8:1፣ 15-17፣ 1 ኛ ቆሮንቶስ 1:30፣ 6:11፣ 2 ኛ ቆሮንቶስ 5:17-21፣ ገላትያ 2:16-21፣ 3:1-14፣ 26፣ 4:4-7፣ ኤፌ 1:6-7፣ 2:1፣ 4-5፣ ፊልጵስዩስ 3:3-9፣ ቆላስይስ 2:13፣ ቲቶ 3 ል 4-7፣1 ኛ ጴጥሮስ 1:23፣ 1 ኛ ዮሐንስ 1:9፣ 3:1-2፣ 9፣ 4:7፣ 5:1፣ 9-13፣ 18)

## X. ክርስቲያናዊ ቅድስና (ሁለንተናዊ መንጻት)

13. ቅድስና ወይም ሁለንተናዊ መንጻት - ከዳግም ልደት በኋላ አማኞች የክርቶስን መልክ ይመስሉ ዘንድ የሚደረግ የእግዚአብሔር ስራ እንደሆነ እናምናለን። በእግዚአብሔር ጸጋ ይኸውም በመጀመሪው ቅድስና ወይም በዳግም ልደት (ከመጸደቅ ጋር በአንድ ወቅት በሚፈጸም) ፣በሁለንተናዊ ቅድስና እና ቀጣይነት ባለው በመክበር የሚጠናቀቅ ፍጹም የሚያደርግ የመንፈስ ቅዱስ ስራ ነው። በመክበር ወደ ልጁ(ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ) መልክ ሙሉ ለሙሉ እንለወጣለን።

ሁለንተናዊ ቅድስና ከዳግም ውልደት በኋላ አማኙ ከመጀመሪያው ኃጢያት ወይም ከአዳማዊ ኃጢያት ተፈጥሮ ነጻ የሚሆንበት እና ለእግዚአብሔር ፈጽሞ ራሱን ወደ መስጠት የሚመጣበትና በፍቅር የሚሆን ቅዱስ መታዘዝ ፍጹም ወደመሆን የሚመጣበት እደሆነ እናምናለን። በመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ወይም ሙላት የሚፈጸም ልብ ከሃጢያት የሚነጻበት በአንድ ልምምድ እና አማኞችን ለኑሮ እና ለአገልግሎት በሚያስችል መንገድ በውስጣችን የሚኖር በመንፈስ ቅዱስ የሚፈጸም ነው።

ሁለንተናዊ ቅድስና ከክርስቶስ ደም የተገኘ ሲሆን ፣አማኙ ባመነ ጊዜ ወዲያውኑ በጸጋው በእምነት የሚፈጸም ሆኖ፣ ከዚህ የሚቀድመው ነገር ፍጹም መሰጠት ነው። ለዚህም የጸጋ ስራና ደረጃ መንፈስ ቅዱስ ምስክርነትን ይሰጣል። ይህም ልምምድ ‹‹ክርስቲያናዊ ፍጹምና››፣ ‹‹ፍጹም ፍቅር›› ፣‹‹ የልብ ንጽህና››፣‹‹የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት›› ፣‹‹የበረከት ሙላት›› ብሎም ‹‹ክርስቲያናዊ ቅድስና›› በሚሉ ሀረጎችና ቃላት ይገለጻል።



14. ንጹህ ልብ - ከበሰለ ባህርይ እንደሚለይ እናምናለን። የመጀመሪያውን ባህርይ ከመቀጽበት

የምታገኘው የሁለንተናዊ ቅድስና ውጤት ሲሆን፣የኋለኛው ባህርይ በጸጋ የማደግ ውጤት ነው።

ሁለንተናዊ ቅድስና እንደ ክርስቶስ ደቀ መዝሙር በጸጋ የማደግ ፍላጎትን ያካትታል። ይሁንና ይህንን ፍላጎት ሆን ብሎ ማሳደግ ፣ክርስቶስን የመምሰልን ባህርይና ስብእና ለማላበስ በሚያስችል መንፈሳዊ ዕድገት መሻሻል ቅድመ ሁኔታዎችና ሂደት ጥንቃቄ የታከለበት ትኩረት መስጠት ያሻል። እንዲህ አይነቱን ጥረት አለማድረግ የአማኙ ምስክርነት ሊያበላሽ፣ ጸጋውም ራሱ ሊጎዳና ሊጠፋ ይችላል። (ኤርምያስ 31:31-34፣ ሕዝቅኤል 36:25-27፣ ሚልክያስ 3:2-3፣ ማቴ 3:11-12፣ ሉቃስ 3:16-17፣ ዮሐንስ 7:37-39፣ 14:15-23፣ 17:6-20፣ የሐዋርያት ሥራ 1:5፣ 2:1-4፣ 15:8-9፣ ሮሜ 6:11-13፣ 19፣ 8:1-4፣ 8-14፣ 12:1-2፣ 2ኛ ቆሮንቶስ 6:14-1-7:1፣ ገላትያ 2:20፣ 5:16-25፣ ኤፌሶን 3:14-21፣ 5:17-18፣ 25-27፣ ፊልጵስዩስ 3:10-15፣ ቆላስያስ 3:1-17፣ 1ኛ ተሰሎንቄ 2:23-24፣ ዕብራውያን 4:9-11፣ 10:10-17፣ 12:1-2፣ 1ኛ ዮሐ. 1:7፣ 9)

(«ክርስቲያናዊ ፍጽምነት፣» «ፍጹም ፍቅር)»፡ ዘዳግም 30:6፣ ማቴዎስ 5:43-48፣ 22:37-40፣ ሮሜ 12:9-21፣ 13:8-10፣ 1ኛ ቆሮንቶስ 13፣ ፊልጵስዩስ 3:10-15፣ ዕብራውያን 6:1፣ ኛ ዮሐንስ 4:17-18
«ያልብ ንጽህና» ማቴዎስ 5:8፣ የሐዋርያት ሥራ 15:8-9፣ 1ኛ ጴጥሮስ 1:22፣ 1ኛ ዮሐንስ 3:3
«የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ወይም ሙላት» ኤርምያስ 31:31-34፣ ሕዝቅኤል 36:25-27፣ ሚልክያስ 3:2-3. ማቴዎስ 3:11-12፣ ሉቃስ 3:16-17፣ የሐዋርያት ሥራ 1:5፣ 2:1-4፣ 15:8-9፣
«የበረከት ሙላት»፡ ሮሜ 15:29
«ክርስቲያናዊ ቅድስና«፡ ማቴዎስ 5:1-7:29፣ ዮሐንስ 15:1-11፣ ሮሜ 12:1-15:3፣ 2ኛ ቆሮንቶስ 7:1፣ ኤፌሶን 4:17-5:20፣ ፊልጵስዩስ 1:9-11፣ 3:12-15፣ ቆላስይስ 2:20-3:17፣ 1ኛ ተሰሎንቄ 3:13፣ 4:7-8፣ 5:23፣ 2ኛ ጢሞቴዎስ 2:19-22፣ ዕብራውያን 6:1፣ 1ኛ ጴጥሮስ 1:15-16፣ 2ኛ ጴጥሮስ 1:1-11፣ 3:18፣ ይሁዳ 20-21)

## XI. ቤተ ክርስቲያን

15. በኢየሱስ ክርስቶስ ጌትነት የሚያምን ማህበረሰብ፣ የአማኞች ህብረት፣ በክርስቶስ አዲስ ቃል ኪዳን የተደረገለት ህዝብ፣ በቃልና በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት በአንድነት የተጠራ የክርቶስ አካል በሚገለጽባት ቤተ ክርስቲያን እናምናለን።

እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያንን በመንፈስ ቅዱስ ህብረትና አንድነት ሕይወቷን እንድትገልጽ ጠርቷታል።ይህም የቃል ስብከት የሚገኝበትን አምልኮ፣ የቅዱስ ቁርባንና የጥምቀት ሥርዓት ለክርስቶስ በመታዘዝ፣ ቅዱስ አኗኗርና በጋራ ተጠያቂነት በስሙ የሚካሄድን አገልግሎት ያጠቃልላል።

በዓለም ውስጥ የቤተ ክርስቲያን ተልዕኮ (በተቀደሰ አኗኗር፣የወንጌል ስርጭት፣ደቀ መዝሙርነት አገልግሎት) በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት የክርስቶስን የማዳን ስራ መቀጠል ነው። ቤተ ክርስቲያን ተልዕኮዋን የምትፈጽመው በወንጌል ስርጭት፣ በትምህርት፣ርህራሄን በማሳየት፣ለፍትህ በመቆም እና ለእግዚአብሔር መንግስት ምስክር በመሆን ደቀ መዛሙርትን በማፍራት ነው።

ቤተ ክርስቲያን ለአካባቢዋ ባህል በሚስማማ መንገድ ራሷን የምታደራጅ ታሪካዊ ተቋም ስትሆን፣ እንደአካባቢያዊ ማህበረ ምዕመናን እንደ አለም አቀፋዊ አካል ህልውናዋን ጠብቃ ትኖራለች። ቤተ ክርስቲያን እግዚአብሔር ለተወሰነ አገልግሎት የጠራቸው ሰዎች ለይታ ትሾማለች።

እግዚአብሔር ቤተ ክርቲያንን በክርስቶስ ምጽአት የሚጠቃለለውን ዘመን እየተጠባበቀች በአገዛዙ ስር እንድትኖር ይጠራታል።

ዘጸ 19፡3፤ኤር 31፡33፤ማቴ 8፡11፣10፡17፣ 16 ፡13-19፣24፣18፡15-20፣28፡19-20፣ዮሐ 17፡14-26፣20‹21-23፣ሐዋ 1፡7-8፣ 2፡32-47፣6፡1-2፣13፡1፣ 14፡23፣ ሮሜ 8፡28-29፤ 4፡16፣ 10፡9-15፣ 11፡ 13-32፣ 12፡ 1-8፤ 15፡1-3፤ 1ኛ ቆሮ 3፡5-9፣ 7፡17፤ 11፡1፤ 17-33፣ 12፡3 12፡3፣ 12፡31፣14‹26-40 ፤2ኛ ቆሮ 5፡11-6፡ 1፤ ገላ 5፡6፤ 13-14፤ 6፡1-5፤ 14 ፤ኤፌ 4፤1-17፤ 5፡ 25-27፤ ፊሊ 2፡1-16፤ 1ኛ ተሰ 4፡1-12፤ 1ኛ ጢሞ 4፤13 ፣ ዕብ 10፡ 19-25 ፤ 1ኛ ጴጥ 1፡1-2 ፣13፤ 2፡4-12፣ 21፤ 4፡1-2፣ 10-11፤ 1ኛ ዮሐ 4፡17 ፤ይሁዳ 24 ፤ራዕ 5፡9-10

## XII. ጥምቀት

16. ጌታችን እንድንፈጽም ያዘዘን ክርስቲያናዊ ጥምቀት የኢየሱስ ክርስቶስ የስርየት በረከቶችን ለማግኘት የሚያስችል ቁርባን በመፈጸም የኢየሱስ ክርስቶን አዳኝነት፣ እንዲሁም የቅድስናን የጽድቅን ሙሉ የመታዘዝ ዓላማ ሊመሰክሩ እንደሚገባ እናምናለን።
ጥምቀት የአዲስ ኪዳን ምልክት ስለሆነ፣ ትናንሽ ልጆች ሊጠመቁ ይችላሉ። ይህም የሚሆነው ተገቢውን ክርስቲያናዊ ትምህርት የሚሰጧቸው ወላጆች ወይም አሳዳጊዎች ለማስጠመቅ ሲጠይቁ ነው።
የጥምቀት ሥነ ሥርዓቱ እንደ ጠያቂው ፍላጎት ውሀን በመርጨት፣ በማፍሰስ ወይም በመድፈቅ ሊካሄድ ይችላል።

(ማቴ 3፡1-7፣ 28፡16-20፣ ሐዋ 2፡37-41፣ 8፡ 35-39፤ 10 44-48፤ 16፡29-34፤ ሮሜ 6፡3-4፤ ገላ 3፡ 26-28፤ቆ 212 1ኛ ጴጥ 3፡18-22)

7

## XIII. ቅዱስ ቁርባን (የጌታ እራት)

17. ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የመሰረተው መታሰቢያና የጌታ እራት የመስዋዕትነት ሞቱን የሚያውጁ ወሳኝ አዲስ ኪዳን ሥርዓት እንደሆነ እናምናለን። ይህም አማኞች ሕይወትንና ደህንነትን ፣ብሎም በክርስቶስ አማካይነት የመንፈሳዊ በረከቶች ሁሉ ተካፋዮች እንዲሆኑ የሚያደርግ ነው። ቅዱስ ቁርባን የሚሰጠው በተለይ ጠቀሜታውን ለመገንዘብ ለተዘጋጁት ሲሆን፣እነርሱም ጌታ እስኪመጣ ድረስ ሞቱን ለመመስከር ይጠቀሙበታል። ይህ የአማኞች የህብረት ግብዣ ስለሆነ ፣መጋበዝ ያለባቸው በክርስቶስ የሚምኑና ለቅዱሳን ፍቅር ያላቸውን ብቻ ናቸው።

ዘጸ 12 ፡1-14፤ማቴ 26፡26-29፤ ማር 14፡22-25፤ ሉቃ 22፡17-20፤ዮሐ 6፡28-58፤ 1ኛ ቆሮ 10፡14-21፤ 11፡23-32)

## XIV. መለኮታዊ ፈውስ

መጽሀፍ ቅዱስ ስለመለኮታዊ ፈውስ የሚያስተምረውን እውነት በማመን አባሎቻችን ለበሽተኞች የእምነት ጸሎት እንዲያደርጉ እናደፋፍራለን። በተጨማሪም፣ እግዚአብሔር በሐኪሞች አማካኝነት ሰዎችን እንደሚፈውስ እናምናለን።

## XV. የክርስቶስ ዳግም ምጽአት

19. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም እንደሚመጣ እናምናለን። በዚያን ጊዜ በህይወት የምንኖረው ሞተው የቆዩትን አንቀድማቸውም፤ ነገር ግን በርሱ ከጸናን ከሞት ከሚነሱት ቅዱሳን ጋር ሆነን ጌታን በአየር ላይ ለመቀበል እንነጠቃለን። ከዚያም ለዘላለም ከጌታ ጋር እንኖራለን።

ማቴ ፡25፡31-46፤ ዮሐ 14፡1-3፤ ዮሐ 1፡9-11፤ ፊሊ 3፡20-21፤1 ኛ ቆሮ 4፡13-18፤ ቲቶ 2፡11-14፤ዕብ 9፡26-28፤ 2 ኛ ጴጥ 3፡3-15፤ ራዕ 1፡7-8፤ 22፡7-20)

## XVI. የሙታን ትንሳኤ ፍርድና የዘላለም ሕይወት

20. ኃጢተኞችም ሆኑ ጻድቃን ከሞት ተነስተው ከመንፈሳቸው ጋር እንደሚገናኙ እናምናለን። ‹‹ መልካም ያደረጉ ለሕይወት ይነሳሉ። ክፉም ያደረጉ ለኩነኔ ይነሳሉ››

21. ወደፊት እያዳንዱ ሰው በእግዚአብሔር ፊት ቀርቦ ፍርድን እንደሚቀበል። ክፉም ያደረጉ ለኩነኔ ይነሳሉ።

22. ጌታቸን ኢየሱስ ክርቶስን ያመኑትና በታዛዥነት የተከተሉት ሁሉ የከበረ ዘላለማዊ ሕይወት እንደሚያገኙ እናምናለን። እስከመጨረሻ ንሰሀ ያልገቡት ደግሞ በሲኦል ውስጥ ይሰቃያሉ።

(ዘፍ 18፡25፤ 1 ኛ ሳሙ 2፡10፤ መዝ 50፡6፤ ኢሳ 26፡19 ዳን 12፡2-3፤ ማቴ 25፡31-46፤ ማር 9፡43-48፤ ሉቃ 16፡19-31፤ 20 ፡27-38 ፤ዮሀ 3፡ 16-18፤ 5፡25-29፤ 11፡ 21 -27፤ ሐዋ 17፡30-31፤ሮሜ 2፡ 1-16፤14፡712፤ 1 ኛ ቆሮ 15፡12-58፤ 2 ኛ ቆሮ 5፡10፤ 2 ኛ ተሰ 1፡5-10 ራዕ 20 11-15 ፤22፡1-15)

<u>ማጠቃለያ - ለቤተ ክርስቲያን አባላትና አገልጋይ የተሰጠ መመሪያ</u> - ኢየሱስ ክርስቶስን እንደግል አዳኛቸው ተቀብለው፣ ከናዛሪን ቤተ ክርስቲያን ጋር ለመዋሀድ ህብረት ማድረግ የሚፈልጉ ሁሉ በመንፈሳዊ አኗኗራቸውና በተቀደሰ አካሔዳቸው መዳናቸውን ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል። የእግዚአብሔር ቃልም እንዴት መኖር እንዳለብን መመሪያ ይሰጠናል። የቤተ ክርስቲያን አባላት እነዚህን ነገሮች ማድረግ ይጠበቅባቸዋል።